# በኢትዮጵያ አለምአቀፍ የሰላምና ልማት ኢንስቲትዩት የተመራ ልዑክ በካይሮ ተወያየ



አዲስ አበባ፣ ሰኔ 16፣ 2005 (ኤፍ.ቢ.ሲ) በኢትዮጵያ አለምአቀፍ የሰላምና ልማት ኢንስቲትዩት የተመራ ልዩ ልዑክ በኢትዮጵያና ግብፅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ለመምከር ካይሮ ገባ።

በኢትዮጵያ አለምአቀፍ የሰላምና ልማት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር የሚመራው ይኸው ልዑክ ፥ ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር መስሪያ ቤት የተወከሉ ሀላፊዎችን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት ሃላፊዎችን ያካተተ ነው።

ልዩ ልዑኩ ከግብፅ የውጪ ጉዳይ ካውንስል በቀረበለት ጥሪ መሰረት ግብጽ መግባቱን ነው የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ቃል አቀባይ አምባሳደር ባድር አብድል አቲ ያስረዱት።

ቃል አቀባዩ ቀደም ሲል የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ ሙሀመድ ካመል አሚር ከኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ቴዎድሮስ አድሃኖም ጋር ኢትዮጵያና ግብፅ ግድቡ በግብፅና በሱዳን ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅእኖ እንዲገመግም የተቋቋመው ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን ያስቀመጣቸውን የመፍትሄ አሳቦች መተግበር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመነጋገር መስማማታቸውን አስታወሰው ፥ ኢትዮጵያና ግብጽ በናይል ወንዝ ላይ በትብብር ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት ማሳየታቸውን አድንቀዋል።

በግብጽ የኢትዮጵያ አምባሳደር መሀመድ ድሪር በበኩላቸው ኢትዮጵያ ከመጀመሪያ ጀምሮ በግድቡ ዙሪያ ያላትን አቋም ግልጽ ስታደርግ መቆየቷን በማስታወስ ፥ የህዳሴው ግድብ ግብጽንም ሆነ ሱዳንን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት እንጂ የሚጎዳ አለመሆኑን አስረድተዋል።

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የግብፅ አምባሳደር ሞሃመድ እድሪስ *"ለኢትዮያውያን እህትና ወንድሞቹ መግለፅ የምፈልገው እኛ ግብፃውያን ከኢትዮጵያ ልማት ጎን መሆናችን ነው ፡፡ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ተመስርቶ የመጣን መንኛውንም ፕሮጀክት እንደግፋለን"* ማለታቸውን የዘገበው ዴይሊ ኒውስ ኢጅፕት ጋዜጣ ነው።